School of Dental Medicine
UNIVERSITY OF COLORADO ANSCHUTZ MEDICAL CAMPUS

አጠቃላይ ስለጥርስ ህክምና ተገቢ መረጃ ላይ የተመሰረተ የህክምና ስምምነት

እንኳን በደህና መጡ፡፡ በUniversity of Colorado School of Dental Medicine (CUSDM) ፍላጎት ስላሳዩ እናመሰግኖታለን፡፡ የ School of Dental Medicine ለራሳችን የጥርስ ተማሪዎች፣ ለአለማቀፍ ተማሪዎች፣ ለድህረ ምረቃ ተማሪዎች እና ለነዋሪዎች የጤና ትምህርት እየሰጠ፣ በተጨማሪ ለብዙ ታካሚዎች ደግሞ የጥርስ ህክምናን ለማቅረብ ችሏል፡፡

አጠቃላይ መረጃ:

የThe University of Colorado School of Dental Medicine ለታካሚዎች ካለ አንዳች የዘር፣ ቀለም፣ የትውልድ መነሻ፣ እርግዝና፣ ፆታ፣ እድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣ የሀይማኖት፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት አመለካከት፣ የፆታ ማንነት፣ የፆታ አገላለፅ፣ የጡረታ ሁኔታ፣ የፖለቲካ ዝንባሌ ወይም የፖለቲካ ፍልስፍና ልዩነቶች በሽተኞችን ይቀበላል፡፡

የሕክምና ማስተማር መቸት: ተማሪዎች እና ወይም ሬዝደንቶች በ Dental Faculty Practice (DFP) ከሚሰጠው ህክምና በስተቀር፣ ሁሉንም የህክምና አገልግሎቶችን ይሰጣሉ፡፡ በተማሪዎች እና ወይም በሬዝደንቶች የሚቀርበው የህክምና አገልግሎት በህክምና ምርመራ አስተማሪ አባላቶች የበላይ ተቆጣጣሪነት ነው፡፡ በአንዳንድ የተወሰኑ የጥርስ ህክምና ውስብስብነት ምክንያት የተነሳ: ሁሉም ታካሚዎች በትምህርት ግቢ ቤቱ ውስጥ ሊታከሙ አይችሉም፡፡ ተማሪዎች/ሬዝደንቶች የህክምና ምርመራን ለማጠናቀቅ ከግሉ የጥርስ ህክምና ዘርፍ የበለጠ ግዜ ይፈልጋሉ፡፡

የታካሚዎች/ የአቅራቢ መገኘት: በምሁራን ማህበር መስፈርቶች ምክንያት በማስተማሪያ ክሊንኮች ውስጥ የተማሪ፣ የሬዝደንቶች እና የፋካሊት መገኘት ውስንነት አለ፡፡ ታካሚዎች ሊቀየር የሚችል መርሀ ግብር በማውጣት እና ቀጠሮአቸውን የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡ ቀጠሮን ለመቀየር ወይም ለመሰረዝ ደግሞ ቢያነስ ከ48 ሰዓት በፊት ለተማሪ/ ለሬዝደንት የማሳወቅ ግድ ነው፡፡ ቀደም ብሎ ሳያሳውቁ ከሁለት ግዜ በላይ ቀጠሮን ያሳለፉ ታካሚዎች፣ ወይም ወሳኝ የቀጠሮ መርሀ ግብራቸውን መጠበቅ ያልቻሉ ታካሚዎች (በተደጋጋሚ ብዙ ቀጠሮዎችን ከሰረዙ፣ ለቀጠሮዎች አርፍዶ የሚገኙ እና የመሳሰሉት) ህክምናቸው ሊቋረጥ ይችላል፡፡

የታካሚ መለያ: CUSDM የታካሚዎቻችንን የግል መረጃ ደህንነት ለማረጋገጥ የሚረዱ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡ ይህም ሂደት ታካሚዎች ወደ CUSDM በሚመጡበት ወቅት የሁሉንም ማንነት በማረጋገጥ የሚከናወን ነው፡፡ ሁሉም ታካሚዎች በእያንዳንዱ ቀጠሮ ፎቶ ያለበት ህጋዊ መታወቂያ ለምሳሌ የኮሎራዶ የመንጃ ፈቃድ፣ የኮሎራዶ የመታወቂያ ካርድ፣ ፓስፖርት ወይም ሌላ በመንግስት የተሰጠ መታወቂያ እንዲያሳዩ ይጠየቃሉ፡፡ በተጨማሪም ሁሉም ታካሚዎች ለሚከናወነው የህክምና መለያነት በመጀመሪያ ቀጠሮአቸው ፎቶግራፍ ይነሳሉ፡፡

የአስተርጓሚ አገልግሎቶች: ታካሚዎች በSchool of Dental Medicine በሚያደርጉት የህክምናቸው ሂደት ወቅት ከጠየቁ: CUSDM ነፃ የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ያቀርባል፡፡ ይህ የአስተርጓሚ አገልግሎት የሚያካትተው: የኢንግሊዝኛ ቋንቋን መናገር ወይም መረዳት ለማይችሉ እንዲሁም የመስማት እና የማየት ችግር ያላቸውን ነው፡፡

የገንዘብ እና የክፊያ አገልግሎቶች: አገልግሎቶች የሚቀርቡት በህክምናው በተጓዙት መሰረት ባደረገ ክፍያ ሂደት ነው፡፡ ከተመረጡት የጥርስና የመንጋጋ ህክምና በስተቀር: የክፍያ እቅዶች አይተገበሩም፡፡ ታካሚዎች ለአገልግሎቶቹ በቀጠሮአቸው ወቅት ክፊያን እንዲፈፅሙ ይጠበቃሉ፡፡ ክፊያን አለመፈፀም ደግሞ የቀጠሮ(ዎችን) መሰረዝ ወይም እንደገና መቀጠርን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ገንዘብ፣ የግል ቼኮች፣ ቪዛ፣ ማስተር ካርድ፣ ድስከቨር፣ እና አሜሪካን ኤክስፕሬስ ተቀባይነት ካላቸው የክፊያ ዘዴዎች መካከል ናቸው፡፡ የኢንሹራንስ ክፊያዎች እና Medicaid ተቀባይነት አላቸው፡፡ ነገር ግን በኢንሹራንስ የማይሸፈኑ ክፊያዎች የታካሚው ሀላፊነቶች ሲሆኑ በአገልግሎቱ ወቅት መከፈል አለባቸው፡፡

ድንገተኛ አገልግሎቶች: በፕሮግራሞቻችን ውስጥ ጥሩ ተሞክሮ ላስመዘገቡ ታካሚዎች CUSDM ድንገተኛ አገልግሎትን ያቀርባል፡፡ በአሁኑ ወቅት በፕሮግራሞቻችን ውስጥ እየተሳተፉ ላልሆኑት ታካሚዎች ድንገተኛ አገልግሎትን መሰረት ባደረገ ክፊያ ለድንገተኛ እና ለአስቸኳይ ህክምና እንክብካቤ በመጡ ታካሚዎች ይቀርብላቸዋል፡፡ ክፊያዎች በሙሉ የህክምና አገልግሎቱ በሚቀርብበት ወቅት መከፈል እንዳለበት እና የሚሰጠው አገልግሎትም አስኳቸይ (ታካሚውን ለድንገተኛ ህክምና ምክንያት የሆነው ነገርን መለየት) ላይ ብቻ የተገደበ እና ተገቢ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ህመምን እና ወይም እንፌክሽንን የመቆጣጠር አገልግሎት አገልግሎት ላይ ብቻ የተወሰነ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

የተወሰነ የህክምና አገልግሎት: ለተወሰነ የጥርስ ህክምና የተላኩ ታካሚዎች በሪፈራል መዝገቡ ላይ ለተጠቀሱት ጥርስ/ጥርሶች ህክምና ብቻ ተቀባይነት ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል፡፡ ይህም ብቸኛው የሚቀርበው ህክምና ሲሆን ተጨማሪ የጥርስ ህክምና ሪፈር በሚደረግለት የጥርስ ሀኪም የሚሰጥ ይሆናል፡፡ ታካሚዎች የተዘረዘሩትን የክፊያ ፖሊስዎችን እንዲከተሉ ይጠየቃሉ፡፡ ተጨማሪ የጥርስ ህክምና የሚያስፈልግ ከሆነ ታካሚው ሌላ ሪፈራል ወይም ለአፍ ምርመራ ክፊያ መፈፀም ይጠበቅበታል፡፡

የሚስጥር አሰራሮች ማስታወቂያ (Notice of Privacy Practices): CUSDM በ "Notice of Privacy Practices" መሰረት፣ መረጃዎችን ለሌሎች ተቋማት ወይም የጤና አገልግሎት አቅራቢዎች፣ ለህክምና፣ ለአገልግሎቶች ክፊያ እና ለጤና እንክብካቤ ስራዎች ይፋ ሊያርግ ይችላል፡፡

ሕክምናን የማቋረጥ መብት: CUSDM ለየትኛው ተገቢ ለሆነ ምክንያት፣ እንደ ቀጠሮን በብዛት ሳይገኙ መቅረት፣ አስቸጋሪ የግለሰቦች ባህርይ፣ ወይም የታዘዙትን ህክምናዎችን ሳያሟሉ በመቅረት ምክንያቶች ህክምናን የማቋረጥ መብት አለው፡፡ እንደነዚህ ባሉት አጋጣሚዎች፣ ታካሚው ወይም የታካሚው ተወካይ አማራጭ ሙያዊ የጥርስ ህክምናን ለመከታተል ሙሉ ሀላፊነቱን ለመውሰድ ይስማማሉ፡፡ ታካሚው ህክምናው መቋረጡን እንዲያውቅም ደብዳቤ ይላክለታል፡፡ ማንኛውም ከህክምናው እና ምርመራዎቹ ጋር የተያያዙት ማህደሮች በሙሉ የ CUSDM ንብረቶች ናቸው፡፡ ማህደሮቹ እና የኤክስ ሬይ ውጤቶች በፅሁፍ ከተጠየቁ በተመጣጣኝ ዋጋ ሊባዙ ይችላሉ፡፡ ህክምናው የተቋረጠ ከሆነ፣ CUSDM ህክምናው ለመቋረጡ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ለ45 ቀናት የድንገተኛ አገልግሎት፣ ክፊያን መሰረት ያደረገ አገልግሎትን ሊሰጥ ይችላል፡፡

የጥርስ ህክምና አደጋዎች: በህክምና ሂደቶች ሊያጋጥሙ የሚችሉ አደጋዎችን አሰመልከቶ ማንኛውንም ጥያቄ ለመመለስ በCUSDM ራሱን የቻለ ፋካሊቲ አለ፡፡ ሁሉም የጥርስ ህክምና ሂደቶች፣ ከተወሰኑ የሚወሰዱ መድሃንቶች አማካኝነት ሊከሰቱ የሚችሉ ተፅእኖዎችን ጨምሮ ሁሉም የተወሰነ አደጋዎች አሏቸው፡፡ አደጋዎቹ የሚያካትቱት: የአለርጂ ምልክቶች፣ ቁስል/የተላጠ ገላ፣ የተቆጣ/ሰንበር ያወጣ ገላ፣ እና የጥርስ ህመም፡
፡

አጠቃላይ ስለጥርስ ህክምና ተገቢ መረጃ ላይ የተመሰረተ የህክምና ስምምነት

ይህ የህክምና ስምምነት የሚያጠቃልለው:

- የሀገር ውስጥ ማደንዘዣ እና መድሃንቶች
- ራዲዮግራፎች: ፎቶግራፎች
- ጥርስን መንቀል
- ማደስ እና ስርን መትከልን ጨምሮ የጥርስ እጥበት
- የጥርስ ሙሽራዎች
- የጎደለ ጥርስን መሙላት
- ጥርስን በሙሌት ማደስ
- የጥርስ ስር
- ሰው ሰራሽ ጥርስ
- የጥርስ ተከላ
- የጥርስ ቀዶ ህክምና
- ሌሎች

ለማንኛውም ወይም ከላይ ለተጠቀሱት የህክምና ሂደቶች በሙሉ የተለየ በመረዳት ላይ የተመሰረተ ስምምነት እንደሚሰፈልግ እረዳለሁኝ፡፡ በማንኛውም የተራዘመ ህክምና ሁኔታ ምክንያት እና እኔ እንደ ግለሰብ የግል ማንነቴን፣ ምን ሊሆን እንደሚችል ወይም ማንኛውንም የጥርስ ህክምና ስኬትን ማንም መተንበይ እንደማይቻል እረዳለሁኝ፡፡ የጥርስ ህክምና ዋሰትና፣ ማስያዣ ወይም ለስኬቱ ማረጋገጫ እንደሌለው እረዳለሁኝ፡፡ የእያንዳንዱ ሰው ጉዳይ ውጤቱን ለመተንበይ መገመት ቀላል አይደለም፡፡ በተጨማሪም ውጤቱ ሙሉ እንደማይሆን፣ በአጠቃላይ ህክምናው ከተጠናቀቀ ቦኋላ አርክ እንደማይሆን እንዲሁም ሁኔታዬ ተመሳሳ ሊሆን እንደሚችል፣ የተሻለ ወይም የባሰ ሊሆን እንደሚችል እረዳለሁኝ፡፡

የ CUSDM ፖሊሲዎችን አስመልክቶ ጥያቄዎችን ለመጠየቅ እድል አግኝቻለሁኝ፡፡ እነዚያም ጥያቄዎቼ በተገቢ እና በሚያፈካ ሁኔታ ተመልሰውልኛል፡፡

የ CUCSDMን የበሽተኛ መብቶች እና ሀላፊነቶችን ተቀብያለሁኝ፡፡

ስለጤናዬ፡ ጭንቅላቴ፡ እና የጥርሴ ጤንነት ጉዳዮችን አስመልክቶ ትክክለኛ ሪፖርቶች ተሰጥተውኛል፡፡

የአፌን እና የፍቴን አቀማመጥ ፎቶዎች፣ ስላይዶችን፣ ድምፀ መቅረፆችን፣ ሞዴሎችን፣ የአፍ ውስጥ ራጆችን እና ኤክስሬይዎችን እንዲሁም የተነቀሉ ጥርሶቼን እንዲወስዱ ተስማምቻለሁኝ፡፡ የታካሚውን ማንነት የማይለዩ መረጃዎች፣ የአፌን እና የፍቴን አቀማመጥ ፎቶዎች፣ ስላይዶችን፣ ድምፀ መቅረፆችን፣ ሞዴሎችን፣ የአፍ ውስጥ ራጆችን እና ኤክስሬይዎችን እንዲሁም የተነቀሉ ጥርሶቼን ለህትመት፣ ለትምህርት፣ ለሳይነሳዊ እና ለምርምር ተግባራት እንዲወስዱ ተስማምቻለሁኝ፡፡ እኔ በምርምር ጥናቶች ውስጥ ለመሳተፍ ወደ ፊት እንዲያገኙኝ ለ CUSDM ስምምነቴን ሰጥቻለሁኝ፡፡

የጥርስ መረጃዬን ኮፒ ራዲዮግራፎችን ጨምሮ፣ በሚያስፈልግበት ወቅት ለሪፈራል የጥርስ ሀኪም እንዲላክ ለCUSDM ስምምነቴን ሰጥቻለሁኝ፡፡

Revised 08/05/2019

School of Dental Medicine
UNIVERSITY OF COLORADO ANSCHUTZ MEDICAL CAMPUS

አጠቃላይ ስለጥርስ ህክምና ተገቢ መረጃ ላይ የተመሰረተ የህክምና ስምምነት

የቀጠሮዎቼን ቀን እና ሰዓት እንዲሁም ሌሎች አጠቃላይ የቀጠሮ መረጃን ለማስታወስ ኢሜልን፣ አጭር የፅሁፍ መልዕክትን እና የስልክ ማስታወቂያዎችን በመጠቀም እንዲያገኙኝ ለCUSDM ስምምነቴን ሰጥቻለሁኝ፡ ፡ ማስታወቂያዎችን ለመቀበል ላልስማማ እችላለሁኝ፡፡

በቁጥጥር ስላለ ስለሚገኝ የመድሃኒት አይነት ከሆነ፣ ፋርማሲ ላይ ይህንን ማዘዣ በሚሞለበት ወቅት የመንግስት ህግ የተወሰነ የማዘዣውን መረጃ፣ ስሜን ጨምሮ፣ በተጠበቀ የመረጃ ዳታ ቤዝ ውስጥ እንዲገባ (የኮሎራዶ የመድሃንት ማዘዣ ቁጥጥር ፕሮግራም) ሊጠይቅ እንደሚችል እረዳለሁኝ፡፡ ስልጣን የተሰጣቸው የተከለከሉ መድሃንቶችን የሚያዙ እና ህግ አስፈፃሚዎች በተወሰነ ሁኔታዎች ውስጥ ለተፈቀደ ፍጆታ ዳታ ቤዙን ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

የ University of Colorado School of Dental Medicine ፋካሊቲ፣ ሬዝደንቶች እና ተማሪዎች ለኔ ወይም በዚህ ፎርም ላይ ለተዘረዘሩት ልጆችየድንገተኛ ህክምናን እንዲሰጡ ስልጣን ሰጥቻለሁኝ፡፡

ከላይ በዚህ ሰነድ ላይ ያሉት የታካሚው መረጃዎች በሙሉ በመረዳት በቅድመ ተከተሉ ሂደቶች በሙሉ እና በተለየ ሁኔታዎች ለመግዛት ተስማምቻለሁኝ፡፡ እኔ ስሜ የተመለከተው፣ ለራሴ እና ለአቅመ አዳም/ሄዋን ልለበቃ/ችና ስሙ/ሟ በዚህ ሰነድ ውስጥ የተጠቀሰ ህፃን ምርመራ እና ወይም ህክምና እንዲያደርግ ለUniversity of Colorado School of Dental Medicine ስምምነቴን ሰጥቻለሁኝ፡፡

ኤሌክትሮንክ ፊርማ መፈረም አለበት

Revised 08/05/2019